# በአካል ተገኝቶ (In-Person) መማር ዕቅድ ላይ እና የአየር ጠባይ ሁኔታ ማስጠንቀቂያዎች ላይ፣ ጠቃሚ የሆነ የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS) አዲስና ማሻሻያዎች (Updates)

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS)፣ የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ሞልቶ ማስገቢያው የመጨረሻ ቀን እስከ አርብ፣ ዲሴምበር (Dec.) 18 ቀን ድረስ አራዝሟል።

የትምህርት ቤት ህንፃዎቻችን እንደገና ለመክፈት እና በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር፤ ከሁሉም ምላሾችን ያላገኘን በመሆኑ እና የምናደርገውን የሽግግር ዕቅድ የተጣራ ለማድረግ ከሁሉም ቤተሰቦቻችን መስማት ያስፈልገናል።

ለእያንዳንዱ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS) ውስጥ የሚማሩ ልጆችዎ፤ በድብልቅ (hybrid) መማር ወይም 100% በርቀት (virtual) መማር፤ ከሁለቱ የትኛውን እንደሚመርጡ ለማጋራት፣ አሁን፤ እስከ አርብ ዲሴምበር (Dec.) 18 ድረስ ጊዜ አለዎት።

በርቀት (virtual) መማር ወይም በድብልቅ (hybrid) መማር ምርጫዎችዎ ላይ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጠቃሚ የሆኑ አዲስና ማሻሻያዎችም (updates) አሉን።

**በጃንዋሪ (January) መጨረሻ አካባቢ ላይ፣ በአካል ተገኝቶ (in-person) መማር በሚጀመር ጊዜ፣ ተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር ዘዴን ስለመጠቀም የተደረገውን አዲሱን ውሳኔ፤ ከጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር ግሬጎሪ ሃቺንግስ (Superintendent Dr. Gregory C. Hutchings, Jr.) የተሰጠውን የሚከተለውን መልዕክት እባክዎን ይመልከቱ። ተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር ምን እንደሆነ፤ ምን ማለት እንደሆነ፣ እና የቤተሰብ ምርጫ ቅፁን እንዴት ማጠናቀቅ እንደምትችሉ ወይም የምታሻሽሉትን ነገሮች እንዴት ማድረግ እንደምትችሉ እወቁ።**

**ጠቃሚ የሆነ ቪዲዮ: በ[ስፓኒሽ]፣ [አማርኛ] ወይም [አረብኛ] ይመልከቱ።**




**ስለ ቤተሰብ ምርጫ ቅፅ፣ ስለ ድብልቅ መማር ወይም ስለ ተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር፤ ጥያቄዎች አለዎት?**

በይበልጥ ተደጋግመው ለሚጠየቁ ጥያቄዎች፤ አንዳንድ መልሶቻችንን እዚህ ያገኛሉ:

**ድብልቅ (hybrid) መማርን ከመረጥን፤ ልጄ ምን ያህል ቀናት ነው በትምህርት ቤት በአካል ተገኝቶ (in person) የሚማረው?**

ድብልቅ ( hybrid)ን ለሚመርጡ ቤተሰቦች፣ ልጆቻቸው በትምህርት ቤት ተገኝተው (in person) የሚማሩት፣ በሣምንት ሁለት ቀናት ነው።

**ተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር ምንድነው?**

ዕቅዳችን፣ አስተማሪዎች በአካል ተገኝቶ (in-person) ክፍሎቻቸው ውስጥ ተማሪዎችን በቡድን ማስተማር፣ እና እንደዚሁም ደግሞ፤ የርቀት (virtually) ትምህርትንም ጎን ለጎን ማስተማር ነው። ይህ "ተጓዳኝ (concurrent)" ማስተማር ይባላል። አስተማሪው፣ ወይ በክፍል ውስጥ፤ ወይ ደግሞ በመኖሪያ ቤት የሚገኙ ይሆናል።

**ልጄ በአሁኑ ወቅት ከሚያስተምሩት አስተማሪ ጋር መቆየት ይችላል?**

ይህ ተጓዳኝ (concurrent) የማስተማር አቀማመጥ፣ አብዛኞዎቹ ተማሪዎቻችን በአሁኑ ወቅት ካሏቸው አስተማሪ ጋር መቆየት እንዲችሉ ዕድል ይሰጣቸዋል። ይህ በሣምንት ሁለት ቀናቶችን፤ 100% በርቀት (virtual) ለሚማሩ ተማሪዎች እና ወደትምህርት ቤት ሄደው በአካል ተገኝቶ (in-person) ለሚማሩ ተማሪዎች፤ የሚያካትት ይሆናል።

**የተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር፣ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?**

በማንኛውም ጊዜ፣ ተመልሰን 100% በርቀት (virtual) መማር የሚያስፈልገን ሁኔታ ቢፈጠር፣ የተለዋዋጭነት አቅም እንዲኖረን ያደርገናል። አብዛኞዎቹ ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት ካሉት አስተማሪያቸው ጋር እንዲቆዩም ዕድል ይሰጣቸዋል።

**የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ሞልቶ የማጠናቀቂያ የማብቂያው ቀን፣ ለምንድነው ወደ ዲሴምበር (Dec.) 18 ቀን የተራዘመው?**

የትምህርት ቤት ህንፃዎቻችን እንደገና ለመክፈት እና በአካል ተገኝቶ (in-person) ለመማር፤ ከሁሉም ምላሾችን ያላገኘን በመሆኑ እና ዕቅዶቻንን የተጣራ ለማድረግ፤ ከሁሉም ቤተሰቦቻችን መስማት ያስፈልገናል። በዚህ በአዲሱ 'ተጓዳኝ (concurrent) ማስተማር፣ እና አብዛኞዎቹ ተማሪዎች በአሁኑ ወቅት ካላቸው አስተማሪ ጋር መቆየትን አስመልክቶ የተሰጠውን መረጃ በተከተለ፤ ባደረጉት ውሳኔ ላይ ቤተሰቦች ለውጦችን እንዲያደርጉ ዕድል መስጠጥም እንፈልጋለን።

**የቤተሰብ ምርጫ ቅፅን ለእያንዳንዱ ልጆቼ የተለያየ ቅፅ ሞልቶ ማጠናቀቅ ያስፈልገኛል?**

አዎን። የቤተሰብ ምርጫ ቅፅን ለእያንዳንዳቸው ልጆችዎ ሞልተው ማጠናቀቅ ያስፈልግዎታል። ይህም ማለት፤ በድብልቅ (hybrid) ወይም በርቀት ( virtual) መማር ላይ፣ ለእያንዳንዱ ልጅ የተለያየ ውሳኔዎችን ለማድረግ ያስችልዎታል።

**ይህ ቅፅ ሞልቶ ለማጠናቀቅ፣ እርዳታ እንዴት ማግኘት እችላለሁ?**

የ'PowerSchool'ን ለማግኘት ወይም ቅፁን ሞልቶ ለማጠናቀቅ እርዳታ ከፈለጉ፣ እባክዎን የ'Virtual PLUS+ የእርዳታ መስጫ መስመር'ን ይደውሉ።

**በቅፁ ላይ የሰጠሁትን ምላሽ መቀየር እችላለሁ?**

በቤተሰብ ምርጫ ቅፅ ላይ ለውጦች አድርጋችሁ የመጨረሻ ምላሽዎን ለማስቀመጥ እስከ ዲሴምበር (Dec.) 18 ቀን ድረስ ጊዜ አለዎት። ከዚያ በኋላ፣ ለእያንዳንዱ ክፍለጊዜ እና ትምህርት ቤት ዕቅዳችንን ማጣሪያ በምናደርግበት ጊዜ ምላሻችሁን እንጠቀመዋለን።

***ተጨማሪ ለሆኑ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾችን እና ቁልፍ በሆኑ ርዕሶች ላይ የቪዲዮ ቀረፃዎችን፣ በኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS) ድህረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ።***

## የቤተሰብ ምርጫ ቅፅን፣ እንዴት ማጠናቀቅ ይቻላል

ቅፁን ሞልቶ ለማጠናቀቅ ወይም አዲስና ማሻሻያዎችን (update) ለማድረግ፤ ጥቂት አማራጮች ይኖርዎታል:

**በ'PowerSchool Parent Access' ውስጥ፤ የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ (Family Choice Form)ን ሞልተው ያጠናቅቁ።** [ቅፁን የማጠናቀቂያ ትዕዛዛዮችን ይመልከቱ]። ማስታወሻ: ቅፁን ለመሙላት፣ የ'PowerSchool Parent Access' አካውንትን መጠቀም አለብዎት። ቅፁን በተማሪው 'PowerSchool' አካውንት አማካኝነት ሊያገኙት **አይችሉም**። የወላጅ አካውንትን ለመፍጠር (set up ለማድረግ) ወይም የወላጅ አካውንትን ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ፣ የ['PowerSchool Parent Access' ድህረ-ገጽን] ይመልከቱ።

***ወይም***

**የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ (Family Choice Form)ን ሞልቶ ለማጠናቀቅ እርዳታ ለማግኘት፤ የVirtual PLUS+ የእርዳታ መስጫ የስልክ መስመርን፤ ከሰኞ - አርብ፣ ከ 9 a.m. እስከ 4 p.m. ይደውሉ:**

- እንግሊዘኛ: 703-844-1763
- ስፓኒሽ: 703-844-3424
- አማርኛ: 703-927-6866
- አረብኛ: 703-927-7095

***ወይም***

**[የትምህርት ቤትዎን የእንግዳ መቀበያ (front office)] ይደውሉ።**

የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ (Family Choice Form)ን እንዴት ማጠናቀቅ እንደሚቻል በ'PowerSchool Parent Access' ላይ፤ እባክዎን ይህንን ቪዲዮ (በ[እንግሊዘኛ] እና በ[ስፓኒሽ]) ይመልከቱ:




[የቤተሰብ ምርጫ ቅፅ (Family Choice Form)ን፣ ሞልቶ በማጠናቀቅ ላይ ተጨማሪ መረጃዎችን እዚህ ይመልከቱ።]

## ለአየር ጠባይ ማስጠንቀቂያዎች ዝግጁ መሆን — የመገኛ አድራሻዎን ዛሬውኑ ያስተካክሉ (Update ያድርጉ)!

የአየር ጠባዩ እየቀዘቀዘ ባለበት ጊዜ፣ በአሁኑ ወቅት የምትጠቀሙበትን የሞባይል ስልክ ቁጥሮችን እና የኢሜል አድራሻዎች፤ ለትምህርት ቤትዎ ሬጅስትራር በማቅረብ፤ ስለአየር ጠባይ ማስጠንቀቂያዎቻችንን በቴክስት (text) መልዕክት እና በኢሜል ለማስተላለፍ እንዲረዳን፤ እባክዎን ማቅረብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። የሚያስፈልገንን መረጃ በሙሉ ለማስተካከል (updated አድርጎ) ለመያዝ፤ አሁን የተመቻቸ ጊዜ ነው!

በመብራት መጥፋት ምክንያት ወይም በመጥፎ የአየር ጠባይ ሁኔታዎች፣ ሁሉንም የትምህርት ቤት ህንፃዎችን መዝጋት በሚያስፈግበት ጊዜ፣ ምንም ዓይነት የምግብ ማከፋፈል፣ ከዲስትሪክቱ ውጪ መጓጓዣ፣ ወይም የVirtual PLUS+ የልጅ እንክብካቤ ፕሮግራሞች በዚያን ቀን አይኖርም።

የአየር ጠባይ ማስታወቂያዎች፣ በአራት ቋንቋዎች በሚከተሉት መንገዶች ይጋራሉ።

- ACPS ድህረ-ገጽ (መረጃዎች፤ መጀመሪያ እዚህ ይጫናሉ (post ይደረጋሉ))
- ለኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS) ወላጆች/አሳዳጊዎች፤ የቴክስት (Text) መልዕክቶች እና ኢሜሎች
- ACPS በFacebook እና በTwitter
- ACPS የሞባይል አፕ (mobile app)
- ACPS-TV የአካባቢው ኬብል ቻናል (cable channel) 71
- የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ (ACPS) የአስቸኳይ ጊዜ መስመር (hotline): 703-866-5300
- የአካባቢው ሬዲዮ እና ቴሌቪዥን ጣቢያዎች

የአሌክሳንድርያ ከተማ የኤሌክትሮኒክ ዜና (City of Alexandria's eNews) — የማህበረሰብ አባላቶች እና ሠራተኞች፣ ይህን መድረክ (platform) አባል ሆነው እንዲመዘገቡ (subscribe እንዲያደርጉ) አበክረን እናበረታታለን።